የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ መስከረም ፲፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 62.
ADDIS ABABA 24th September, 2008

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፫/፪ሺ ዓ.ም

የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ……… ገጽ ፬ሺ፪፻፹፪

<u>CONTENTS</u>

**Proclamation No. 573/2008**

The Revised Political Parties Registration Proclamation Page 4282

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፫/፪ሺ

## <u>የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ</u>

በሕገመንግሥቱ መሠረት ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመሳተፍ የፖለቲካ ሥልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ በህግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ዜጎች የፖለቲካ ፓርቲ ሲመሰርቱ እና በአባልነት ሲንቀሳቀሱ ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ መሠረታዊ መርሆዎችን በመደንገግ ህጋዊ ሰውነት አግኝተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዋሀድ ወይም ግንባር በመፍጠር ወይም ተቀናጅተው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## <u>ክፍል አንድ</u><br><u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፫/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## <u>PROCLAMATION NO. 573/2008</u>

## <u>POLITICAL PARTIES REGISTRATION PROCLAMATION</u>

**Whereas,** it is necessary to regulate by law the conditions by which citizens using their freedom of association in accordance with the Constitution for participating in peaceful and lawful political activities to assume political power;

**Whereas,** it is necessary, to provide the right and duty of citizens when forming political parties and acting as members of political parties, and also by providing basic principles to be followed by political parties to enable the political parties to act upon having legal personality;

**Whereas**, it is necessary to provide the manner by which political parties able to act by forming union or front or coalition;

**Now, therefore**, in accordance with Article - 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## <u>PART ONE</u><br><u>GENERAL PROVISIONS</u>

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as "The Revised Political Parties Registration Proclamation No. 573/2008."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፤

፩/ “ቦርድ” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፣

፪/ “የፖለቲካ ፓርቲ” ወይም “የፖለቲካ ድርጅት” ማለት ከሕብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንፀባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ማሕበራዊ ተቋም ነው፣

፫/ “ህገ መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ነው፣

፬/ “ንግድና ኢንዳስትሪ ሥራዎች” ማለት ለትርፍ ለሚካሄድ የማምረት፣ አገለግሎት የመስጠት ወይም የማከፋፈል ሥራዎችን ይጨምራል፣

፭/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀፅ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል፣

፮/ “መደበኛ ነዋሪ” ማለት በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም በወጣው የፍተሐብሔር ህግ እንደተደነገገው በመደበኛ የመኖሪያ ቤታ የሚኖር ሰው ነው፣

፯/ “የፖለቲካ ፓርቲ ሃላፊዎች” ማለት እንደ ሁኔታው የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ አባላት፣ ወይም በተመሳሳይ የሥልጣን ደረጃ ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ናቸው፣

፰/ “ውህደት” ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ በህግ መሠረት ተመዝግበው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ላይ ተዋህደው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመሰርቱበት ሁኔታ ነው፣

## 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1) “Board” means the Ethiopian National Election Board;

2) “Political Party” or “Political Organization” means a social institution registered in accordance with this Proclamation organizing underwhich part of the society and having its own political program reflecting its own belief and purpose with a view to hold political power by participating in national or regional political activities in a democratic way;

3) “Constitution” means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

4) “Commercial and Industrial Activities” means an activity taking place for the purpose of profit making and includes production, service rendering and distribution;

5) “Regional State” means a regional state established by Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes for the purpose of this Proclamation Addis Ababa and Dire Dawa administrations;

6) “Resident” means a person residing regularly in a place as provided in the 1960 Ethiopian Civil Code.

7) “Political Party Leaders” means members of the executive of a political party or political leaders at similar level of authority;

8) “Union” means a political party established as a result of a union effected between two or more parties registered in accordance with the appropriate law;

፱/ "ግንባር" ማለት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ህጋዊ ህልውናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ የሆነ ስያሜ፣ የፖለቲካ ፕሮግራም እና መተዳደሪያ ደንብ ኖሯቸው ለመንቀሳቀስ ሲወስኑ የሚደራጅ አካል ነው፣

፲/ "መቀናጀት" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለጊዜያዊ አላማ በጋራ ለመሥራት እያንዳንዱ አካል ህጋዊ ህልውናውን እንደጠበቀ ለመቀናጀ ታቸው ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የሚያገ ኙበት ሁኔታ ነው፣

፲፩/ "መተካት" ማለት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ነባር ስሙንና ፕሮግራሙን በመቀየር አዲስ ስምና ፕሮግራም በማዘጋጀት በዚሁ ስሙ እና ፕሮግራሙ እንዲታወቅ አስፈላጊውን መረጃ ለቦርዱ በማቅረብ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመዘገብበትና የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ነው፣

፲፪/ "የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር" ማለት የሞያ ብቃቱ የተረጋገጠ፣ በማናቸውም መንገድ ከሚሾመው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙ ነት የሌለው በፖለቲካ ፓርቲ የሚሾም ሰው ነው፣

፲፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላው ኢትዮጵያ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት፣ ምዝገባ እና ሰነዶች</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>
### <u>የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት</u>

## ፬. <u>የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት</u>

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው።

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፶፰ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም እድሜው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በዚህ አዋጅ መሠረት የሃገር አቀፍ ወይም የክልል የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው።

9) "Front" means an organization formed by two or more political parties, with out prejudicing each constituent party individual legal existence, decided to have a common name, political program and by law;

10) "Coalition" means when two or more political parties for temporary objective decided to act jointly and received temporary certificate for being coalition with each constituent party individual legal existence;

11) "Substitution" means that by which a political party changes its name and program and after presenting to the Board a new program and name with other necessary information is registered and act as a new political party;

12) "Auditor of Political Party" means a person, having a certified professional competency, designated by a political party as auditor without any relation of whatever to the designating party;

13) "Person" means a natural or juridical person;

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable all over Ethiopia.

## <u>PART TWO</u>
## <u>FORMATION, REGISTRATION AND DOCUMENTS OF POLITICAL PARITES</u>

### <u>CHAPTER ONE</u>
### <u>FORMATION OF POLITICAL PARTY</u>

## 4. <u>Political Party Formation</u>

1) Without prejudice to Article 58 of this Proclamation, every Ethiopian shall have the right to form a political party or to be a member of a political party.

2) Without prejudice to Article 58 of this Proclamation, any Ethiopian aged 18 or above shall have the right to membership, in accordance with this Proclamation, of country-wide or regional political party .

## ፭. አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤

ሀ/ ፩ሺ፭፻ መስራች አባላት ሲኖሩት፣

ለ/ ከነዚህ መስራች አባላት ውስጥ ከአርባ በመቶ /፵ በመቶ/ የማይበልጡት የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣

ሐ/ የተቀሩት መስራች አባላት ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ከሚገኙት ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑና፣

መ/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ /ሐ/ መሠረት ከየክልሉ ለአገር አቀፍ ፓርቲ መስራችነት ከሚመዘገቡት አባላት በእያንዳንዱ ክልል አስራ አምስት በመቶ /፲፭በመቶ/ ሲሆኑ ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ የተጠቀሱት መስራች አባላት ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸው ሆነው፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን በፊርማቸው የገለፁ መሆን አለባቸው።

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው።

## ፮. የክልል የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በክልል የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤

ሀ/ ፯፻፶ መስራች አባላት ሲኖሩት፣

ለ/ ከነዚህ መስራች አባላት ውስጥ ከስልሳ በመቶ /፷በመቶ/ በላይ የሆኑት የክልሉ መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ የተጠቀሱት መስራች አባላት ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸውና የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን በፊርማቸው የገለፁ መሆን አለባቸው።

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው።

## 5. Formation of a Country – Wide Political Party

1) A political party shall be formed as country-wide political party where:

a) it has at least 1,500 founding members:

b) at least forty percent (40%) of its founding members are residents of the same regional state;

c) its remaining founding members are residents of at least four of the Ethiopia regional states; and

d) the number of members registered as founders in each region as laid down in paragraph (c) of this sub - article constitutes at least fifteen percent (15%) of the total founding members.

2) The founding members provided under sub article (1) of this Article shall have to be eligible to vote and their consent to be members of the political party shall be expressed by their signature.

3) The document signed by the founding members in accordance with the proceeding sub article (2) shall be a document open to public.

## 6. Formation of a Regional Political Party

1) A political party shall be formed as a regional political party where:

a) it has at least 750 founding members;

b) more than sixty percent (60%) of the founding members are residents of the same regional state.

2) The founding members provided under sub – article 1 of this Article shall have to be eligible to vote and their consent to be members of the political party shall be expressed by their signature.

3) The document signed by the founding members in accordance with the preceding sub–article (2) shall be a document open to public.

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ

### ፯. ስለምዝገባ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ ብቻ ነው።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በስሙ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፣ የንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ መሆን፣ መሸጥ፣ መለወጥ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ንብረት ማስተላለፍ ወይም አላማውን ተከትሎ ማናቸውም ሕጋዊ ተግባር ማከናወን ይችላል። እንዲሁም ግዴታውን የመወጣት ኃላፊነት አለበት።

### ፰. ለምዝገባ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የምዝገባ ማመልከቻ በፖለቲካ ፓርቲው መሪ ተፈርሞ ለቦርዱ መቅረብ አለበት።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፲፫ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ፅሁፍ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው ፕሮግራም፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፭ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ፣

መ/ የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በኃላፊነት ለመስራት የተስማሙ ለመሆናቸው የሚገልፅ በፊርማቸው የተረጋገጠ ሰነድ፣

ሠ/ መስራቾች የፈረሙበትና ለሕዝብ ይፋ የሆነ ሰነድ፣

ረ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ የተመረጡ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ፣

## CHAPTER TWO
## REGISTRATION OF POLITICAL PARTY

### 7. Registration

1) A political party shall have to operate in Ethiopia only up on registration by the Board and upon receipt of a certificate of legal personality in accordance with this Proclamation.

2) A political party that received legal personality in accordance with sub article (1) of this Article shall be capable to enter in to contractual relations with third parties in its own name, sue and be sued, own or possess property, exchange or sale property or transfer property in any other way, or perform any other legal activities following its purpose. In addition it shall have responsibility to comply with its obligation.

### 8. Application of Registration

1) Application for registration of a political party shall be signed by the party leader and submitted to the Board.

2) The application submitted in accordance with sub-article (1) of this Article shall be accompanied by the following documents:

a) the memorandum of association of the party in accordance with Article 13 of this Proclamation;

b) the political programme of the party in accordance with Article 14 of this Proclamation;

c) the by – laws of the party in accordance with Article 15 of this Proclamation;

d) the names and addresses of the party leaders including the consents of the leaders to act as leaders expressed by their signature in the document;

e) the document signed by founding members and opened to public,

f) the document showing the political party leaders are elected by the general assembly;

ሰ/ የፖለቲካ ፓርቲውን ኦዲተር ስም፣ አድራሻ እና በኦዲተርነት ለማገል ገል የተስማማበት በፊርማው የተረ ጋገጠ ሰነድ።

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፪/ የተዘረዘሩት ሰነዶች ከእያንዳንዱ አምስት ቅጂ ከምዝ ገባ ማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፬/ የምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ ያቀረበ የፖለ ቲካ ፓርቲ፦

ሀ/ የምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ እና

ለ/ በየጊዜው ለሚደረጉ የመሠረታዊ ሰነዶች ማሻሻያ ክፍያ

ይከፍላል።

፭/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፬/ /ሀ/ የተደነገገ ውን ክፍያ የከፈለበት ሰነድ ከምዝገባ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅ ረብ ይኖርበታል።

፮/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፬/ የተደነገገው የክ ፍያ መጠን በቦርዱ ይወሰናል።

፯/ በዚህ አንቀፅ መሠረት የተመዘገበ የፖለ ቲካ ፓርቲ ሰነዶች ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለባቸው።

## ፱. <u>የቦርዱ ኃላፊነት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲዎ ችን የመመዝገብ ሥልጣን የቦርዱ ነው።

፪/ በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ማመልከቻ ባቀረበ አካል ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞ ማቅረብ እንዲችል ቦርዱ የምዝገባ ማመልከቻ መቅረቡን በተለያየ ማስታወቂያ ለሕዝብ ይገልፃል።

፫/ በንዑስ አንቀፅ /፪/ መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ፲፬ ቀን ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ ይኖ ርበታል። ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለአመ ልካቹ ፈቃድ አይሰጥም።

፬/ ቦርዱ ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥ መረጃዎች እንዲቀርብለት እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረግ እንቅስቃሴ ከማን ኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መረጃ ወይም ማብ ራሪያ ሊጠይቅ ይችላል።

g) the document containing the name and address of the political party auditor and the signature of the auditor expressing his consent to serve as auditor.

3) Each documents provided under the preceding sub article (2) shall be accompanied by five copies and submitted together with the application for registration.

4) A party requesting for registration by application shall pay:

a) registration fee, and

b) fee for revision of basic documents made from time to time.

5) Payment made in accordance with sub article (4) (a) of this Article ascertained in a document shall be submitted together with the application for registration.

6) The amount payable under sub article (4) of this Article shall be determined by the Board.

7) The documents of the political party registered in accordance with this proclamation shall be open to the public.

## 9. Responsibilities of the Board

1) The registration of political parties in accordance with this Proclamation shall be the authority of the Board.

2) In order to enable persons having opposition to present such opposition against a political party requesting for registration, the Board shall notify the public as to submission of the application for registration.

3) Any person having opposition pursuant to sub article (2) of this Article shall present such opposition to the Board with in 14 days from the date of notification to the public. Within such period the Board shall not issue permission to the applicant for registration.

4) The Board may require necessary and relevant information for registration including explanation and information from any political party for activities carry out pursuant to this Proclamation.

፭/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ መሠረት የሚቀርብለትን ማመልከቻና አባሪ ሰነዶች ተቀብሎ በመመርመር ሰነዶቹ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት የተሟሉ እና ትክክለኛ መሆናቸውን፣ ፓርቲው ህገመንግሥቱንና ይህን አዋጅ የሚያከብ ርና የሚያስከብር መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም የፖለቲካ ፖርቲውን ዋና ጽሕፈት ቤት በመጎብኘት የምዝገባ ማመልከቻውን በተቀበለ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባውን ፎርማሊቲ አጠናቅቆ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል።

፮/ ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፭/ መሠረት የተመዘገበን የፖለቲካ ፓርቲ አግባብ ሆኖ ባገኘው የብዙኃን መገናኛ ለሕዝብ ያሳውቃል።

፯/ ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፭/ በተቀመ ጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበውን የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ህግ መሠረት እንደመዘገበው ይቆጠራል።

፰/ ቦርዱ የምዝገባ ማመልከቻውን ያልተቀበ ለው የፖለቲካ ፓርቲው ማሟላት ያለበ ትን ሳያሟላ በመቅረቱ ከሆነ ይህንኑ በ፴ ቀናት እንዲያሟላ በጽሁፍ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

፱/ ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲው ያቀረበውን የም ዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ያደረገው እንደ ሆነ ይህንኑ ምክንያት ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል።

፲/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፱/ መሠረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ጉዳዩ በፅሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፲፬ ቀን ውስጥ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። አቤቱታ ያቀረበው አካል ለዚህ ጉዳይ አፈፃፀም ህጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቆጥሮ በፓር ቲው መተዳደሪያ ደንብ ተመርጦ በምዝ ገባ ማመልከቻው ላይ ፈርሞ ያቀረበው የፓርቲው መሪ የፓርቲው ህጋዊ ወኪል እንደሆነ ይቆጠራል።

፲፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲ የቀረበለትን የሰነድ ማሻሻያ መርምሮ መቀበል አለመ ቀበሉን በ፴ ቀናት ውስጥ ለፓርቲው ያሳውቃል።

5) The Board upon receiving the application and documents enclosed therewith submitted to it in accordance with Article 8 of this Proclamation shall examine the documents as are required under this Proclamation that the documents are complete and accurate, that the party respects and cause the respection of the Constitution and this Proclamation, and observing the political party's head office, shall process the formalities of registration and issue to the applicant a certificate of legal personality within three month from the date it received the application.

6) The Board shall notify to the public, by appropriate mass media, the political party registered pursuant to sub article (5) of this Article.

7) Where the Board gives no answer with in the period provided under sub article (5) of this Article, the Board shall be deemed to register the applicant political party in accordance with the provisions of this Proclamation.

8) Where the Board rejects the application because of the unfulfilment of certain conditions by the political party, the Board shall inform the applicant with a written notice to fulfill those conditions within thirty days.

9) Where the Board rejects the application for registration by the political party, the Board shall inform its refusal by a written notice.

10) Where a body finds the decisions of the Board in accordance with sub article (9) of this Article unacceptable, it may petition to the Federal High Court within 14 days it received the notice of such refusal; the body which has petitioned shall be deemed to have legal personality for such purpose and the official elected in accordance with the by-laws of the party and signed on the application for registration shall be deemed the lawful representative of the party.

11) The Board after examining the amended document submitted to it by a political party in accordance with Article 12(2)of this Proclamation shall notify its acceptance or refusal to the party with in 30 days.

፲፪/ ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፲፩/ መሠረት የማሻሻያ ሰነዱን መርምሮ ከተቀበለው ይህንኑ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

፲፫/ ቦርዱ የማሻሻያ ሰነዱን ካልተቀበለው አመልካቹ የፖለቲካ ፓርቲ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ እንደሁኔታው በዚህ ህግ መሠረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

፲፬/ ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴን ይከታተላል ተገቢውን መረጃ ይይዛል።

፲፭/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ በክፍል አምስት ድንጋጌ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲን የገቢ ምንጭ የወጪ ዝርዝር እና ንብረት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህገ ወጥ ድርጊት ተፈጽሞ ሲያገኘውም አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

፲፮/ ቦርዱ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተደረገ ድጋፍና የድጋፍ አጠቃቀም ዝርዝር እና

ለ/ ስለፖለቲካ ፓርቲ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወቅታዊ እና ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል።

፲፯/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፵፯ የተደነገገው የኦዲት ሪፖርት እንደደረሰው ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል።

## ፲. <u>መመዝገብ ስለማይችል የፖለቲካ ፓርቲ</u>

ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምድ ወይም አላማው ያደረገ ማንኛውም ቡድን ወይም አካል በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገብ አይችልም፤

፩/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትን በመጣስ በዘር፣ በሃይማኖት እና በመሳሰሉት ልዩነቶች ላይ የተመሠረተ ጥላቻና ጠላትነት በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና በሕዝቦች መካከል በማስፋፋት ጦርነትና ግጭት መፍጠርን ዓላማ ያደረገ፣

12) Where the Board, upon examination in accordance with sub article (11) of this Article, finds the amended document acceptable it shall publicize the acceptance.

13) Where the Board rejects the amendment, it shall order the applicant party to take necessary corrections and where appropriate, the Board may take measures in accordance with this Proclamation.

14) The Board shall follow up the activity of political parties and record the resulting information.

15) The Board shall, in accordance with the provisions of Part Five of this Proclamation, follow up and oversight the income source, expenditure list and property of a political party; where illegal acts are found the Board shall take the necessary measures.

16) The Board shall present annual and regular report to the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia on:

a) grants of government, in accordance with Article 50 of this Proclamation, to political parties and lists of utilization of such grants; and

b) overall activity of political parties.

17) The Board upon receiving the audit report provided under Article 47 of this Proclamation shall make official to the public; and where it deems necessary it may order inspection.

## 10 . **<u>Political Party Barred from Registration</u>**

A group or body which pursue any of the following objectives or acts shall not be registered as political party:

1) aims to foment conflict and war by preaching hatred and enmity among nations, nationalities and peoples on the basis of differences in race, religion and the like, in violation of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፪/ የፖለቲካ ዓላማውን በትጥቅ ለማራመድ የተደራጀ፣

፫/ መንግሥትን በኃይል ጥሎ ሥልጣን ለመያዝ ዓላማ አድርጎ የያዘ፣

፬/ የውጭ ሀገር ዜጎች አባል የሆኑበት የፖለቲካ ድርጅት፣

፭/ ሕገወጥ ዓላማ ለማካሄድ የተቋቋመ የፖለ ቲካ ድርጅት፣ እና

፮/ ህገ መንግሥታዊ ስርዓቱን በህገወጥ መን ገድ ለማፍረስ የተመሠረተ።

**፲፩. <u>በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ስለማይችል ድርጅት ወይም ማህበር</u>**

የሚከተሉት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዚህ አዋጅ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገቡ አይችሉም፣

፩/ በንግድ ሕግ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት፣ የንግድና ኢንዳስትሪ ስራዎችን ለማከናወን የተቋቋሙ ማሕበሮች ወይም ድርጅቶች፣

፪/ ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ወይም ለበጎ አድራጎት ተግባር የተቋቋሙ ማሕበራት ወይም ድርጅቶች፣

፫/ የብዙሃን የሠራተኛ እና የሙያ ማሕበራት፣

፬/ የመረዳጃ ማሕበራት፣

፭/ የሃይማኖት ድርጅቶች፣

፮/ ዕድርና ዕቁብን የመሳሰሉ ማሕበራዊ ተቋሞች፣

**<u>ምዕራፍ ሶስት</u>**
**<u>ስለ ፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች</u>**

**፲፪. <u>የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች</u>**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉት ዋና ዋና ሰነዶች ይኖሩታል፤

ሀ/ የመመስረቻ ፅሁፍ፣
ለ/ የፖለቲካ ፕሮግራም፣
ሐ/ የመተዳደሪያ ደንብ፣
መ/ የሃብትና ንብረት የገቢና የወጪ ሰነዶች፣

2) organized to advance its political objectives by force of arms;

3) aims to take over political power by overthrowing the government by armed force;

4) having members of foreign nationals;

5) formed for the purpose of pursuing unlawful activities; and

6) formed to break down the Constitutional order by way of illegal means.

**11. <u>Organization or Association Bared from Registration as Political Party</u>**

The following organizations or associations may not be registered as political parties under this Proclamation:

1) associations or organizations formed for the purpose of carrying on commercial and industrial activities pursuant to the Commercial Code or the Civil Code or other relevant laws;

2) associations or organizations formed for non profit making or for welfare purposes;

3) communal associations, trade unions and professional associations;

4) mutual help associations;

5) religious organizations;

6) social formations such as idir, equb, and the like.

**<u>CHAPTER THREE</u>**
**<u>DOCUMENTS OF POLITICAL PARTIES</u>**

**12. <u>Document of Political Party</u>**

1) A political party shall have the following basic documents:
   a) memorandum of association,
   b) political programme,
   c) by – laws,
   d) documents related to ownership, property and revenue and expenditure.

፪/ ከላይ የተጠቀሱ ሰነዶችን ለማሻሻል የፈለገ የፖለቲካ ፓርቲ አስቀድሞ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

**፲፫. <u>ስለፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ፅሁፍ</u>**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት የሚፈልጉ ግለሰቦች መስራች ሆነው ለማደራጀት የፈለጉትን የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋማቸውን የሚገልጹበት የመመስረቻ ጽሁፍ ይኖራቸዋል።

፪/ የመመስረቻ ጽሑፍ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ ይሆናል፤

- ሀ/ የፓርቲውን መጠሪያ ሙሉ ስም እና አህፅሮት ስም፣
- ለ/ የፓርቲውን ዓርማ፣
- ሐ/ የፓርቲውን ዓላማ፣
- መ/ የፓርቲውን የገቢ ምንጭ፣
- ሠ/ ፓርቲው የተመሰረተበትን ቀን እና ዓመተ ምህረት
- ረ/ የፓርቲውን ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አድራሻ፣
- ሰ/ የፕሮግራሙን እና የመተዳደሪያ ደንቡን አወጣጥ ስርዓት፣

፫/ የፓርቲው መመስረቻ ጽሑፍ በመስራች አባላቱ የተፈረመ መሆን አለበት።

**፲፬. <u>ስለፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማው አድርጎ የያዘውን የፖለቲካ እምነት የሚቀርጽበት የፖለቲካ ፕሮግራም ይኖረዋል።

፪/ የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም፤

- ሀ/ ፓርቲው የተቋቋመበትን ዓላማ እና
- ለ/ ፓርቲው ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚንቀሳቀስበትን ስልት የሚገልጽ የተግባር መመሪያ ነው።

**፲፭. <u>ስለፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል። የመተዳደሪያ ደንቡም፤

- ሀ/ አባላቱን የሚቀበልበትን ሁኔታ፣
- ለ/ የአባላቱን መብትና ግዴታ፣
- ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲውን ልዩ ልዩ አካላት እና የስራ ኃላፊነታቸውን፣
- መ/ አባላቱ በፓርቲው ሥራ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ፣

2) A political party wished to amend the documents, provided under sub article (1) of this Article, shall first notify to the Board.

**13. <u>Memorandum of Association of a Political Party</u>**

1) Individuals who desire to establish a political party must have a memorandum of association inwhich they declare the establishment of the type of political party they want to organize.

2) A memorandum of association shall include the following particulars:

- a) the name (designation) of the party in whole and in abbreviation;
- b) the emblem of the party;
- c) the objectives of the party;
- d) the source of income of the party;
- e) the day and year of establishment of the party;
- f) the addresses of the head office and branch offices of the party;
- g) the procedures of issuing the by – laws and programme of the party.

3) The memorandum of association of a political party shall have to be signed by the founding members.

**14. <u>Programme of Political Party</u>**

1) Every political party must have a programme inwhich the political aims it pursues as its objectives are formulated.

2) The programme of political party shall be a directive of action which:

- a) describes the objectives for which it is formed; and
- b) specifies the tactics it adopts for achieving its objectives.

**15. <u>By – Laws of Political Party</u>**

1) Every political party must have its own by laws. Such by – laws shall include the following particulars:

- a) conditions for admission of members;
- b) details of the rights and duties of member;
- c) details of the various organs of the party and description of their respective functions;
- d) the manner of participation of members in the activities of the party;

ሠ/ የፓርቲውን የስብሰባ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፣
ረ/ በአባላቱ ላይ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት እና የሥነምግባር እርምጃ፣
ሰ/ የፖለቲካ ፓርቲው የጉባኤ ስብሰባ የሚካሄድበትን ጊዜና ሁኔታ፣
ሸ/ የፖለቲካ ፓርቲው የሚፈርስበትን ሁኔታ፣
ቀ/ ማንኛውም አባል እኩል ድምፅ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሁኔታን ያካተተ መሆን አለበት።

፪/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፖለቲካ ፓርቲው አባል በዜግነቱ የተረጋገጠለትን መብት የሚቀንስ ወይም የተጣለበትን ግዴታ የሚሽር ሊሆን አይችልም።

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን አዋጅ አንቀፅ ፲፮ እና ከአንቀፅ ፳፯ እስከ አንቀፅ ፴፩ የተደነገጉትን ያገናዘበ መሆን አለበት፣

## ክፍል ሶስት
## የፖለቲካ ፓርቲና የአባላት መብት እና ግዴታ
## ምዕራፍ አንድ
## የፖለቲካ ፓርቲ መብት

### ፲፮. የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ጉዳይ ላይ ስላለው ነፃነት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

፩/ የፖለቲካ ፕሮግራሙንና የመተዳደሪያ ደን ቡን የሚያፀድቅበትንና የሚያሻሽልበትን እንዲሁም ስብሰባ የሚያካሂድበትን ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል።

፪/ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት የፖለቲካ ሥራውን የሚመሩ፣ ውሳኔ የሚ ሰጡ እና የሚያስፈጽሙ የአመራር አካላት ይኖሩታል።

### ፲፯. ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ስለማቋቋም

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ሥራውን ለማካሄድ በሀገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

e) the procedures of convening meetings and passing decisions;
f) details of measures of procedure and code of conduct applicable to members;
g) the time and condition of convening assembly of the political party;
h) conditions for dissolution of the political party;
i) details as to the equality of votes between every member of the political party.

2) Any by – laws of a political party shall not have the effect of abridging the rights of a member of the political party guaranteed to him or releasing him from duties imposed up on him as a citizen.

3) By – laws of every political party shall be drawn consistently with the provisions of Article 16 and from Article 27 to Article 31 of this Proclamation.

## PART THREE
## RIGHT AND DUTY OF POLITICAL PARTY AND MEMBERS

## CHAPTER – ONE
## RIGHT OF POLITICAL PARTY

### 16. Independence of a Political Party in Respect of Its Owen Affairs

Every political party:

1) shall determine in its by – laws the procedures of adopting and amending its political programme and by – laws as well as holding meetings;

2) may have leading organs of the political party to direct, decide on and implement its political activities to be determined inaccordance with its by – laws.

### 17. Establishing Branch Offices

Every political party may establish branch offices anywhere within the country for the purpose of carrying out its political activities.

## ፲፰. ከገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚገኘው ገቢ ላይ ምንም አይነት የገቢ ግብር አይከፍልም።

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በሕግ በተወሰነው መሠረት የገቢ ግብር ሰብስቦ ለመንግሥት ገቢ ከማድረግ ነፃ ነው።

## ምዕራፍ ሁለት
## የፖለቲካ ፓርቲ ግዴታ

## ፲፱. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

፩/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ ቦርዱ ሲጠይቅ በህጉ መሠረት የሚፈለገው የአባላት ቁጥር ያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ የማቅረብ፣

ለ/ ፓርቲዎች ግንባር ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም ለመቀናጀት ሲፈልጉ ቦርዱ በስብሰባቸው ላይ እንዲገኝ ቢያንስ ከ፴ ቀናት በፊት የማሳወቅ፣

ሐ/ በየዓመቱ ወይም ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ፓርቲው በኦዲተር የተረጋገጠ የሃብትና እዳ ሰነድ በፓርቲው መሪ ፊርማ ለቦርዱ የፅሁፍ ሪፖርት የማቅረብ፣

መ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ /ሐ/ የተጠቀሰው ሪፖርት የፖለቲካ ፓርቲውን የገቢ ወይም የሃብቱን ምንጭ የማካተት ግዴታ አለበት።

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ የተደነገገውን ግዴታ ላላሟላ የፖለቲካ ፓርቲ የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በአንቀፅ ፴፱ መሠረት አስፈላጊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

፫/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው መሪ በዚህ አንቀፅ መሠረት ለቦርዱ በፅሁፍ ያሳወቀው ሃብትና እዳ ሃሰት ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ይጠየቃል።

## 18. Exemption From Income Tax

1) Any political party shall not be liable to pay any kind of income tax on income collected from its members and supporters.

2) No political party shall collect and transfer to the government income tax payable inaccordance with the law in respect of the salaries of its employees.

## CHAPTER TWO
## OBLIGATION OF POILITICAL PARTY

## 19. Duty to Submit Report

1) A political party registered in accordance with this Proclamation shall:

a) submit a document showing the required number of members under this Proclamation are complied, where the Board asks;

b) notify the Board before 30 days of the convening of the meeting to present there with, where parties need to form between them front, or union or coalition;

c) submit a written report annually or whenever the Board requires signed by the political leader as to the property and debts of the party certified by auditor;

d) the report provided under sub – article 1(c) of this Article shall include the source of income and property of the political party.

2) The Board shall give a one month period for a political party that does not comply with the obligations under sub article (1) of this Article to fulfill such conditions with in such period, thenafter the Board may take necessary measures pursuant to Article 39 of this Proclamation.

3) Where a political party or a leader of political party informed in writing to the Board as to the property and debt inaccordance with this Article has been found untrue, without prejudice to the provisions of Article 39 of this Proclamation it shall be liable under the appropriate provisions of the Penal Law.

፬/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀፅ /፬/ የተደነገገውን መረጃ ወይም ማብራሪያ ሳይሰጥ የቀረ እንደ ሆነ በዚህ አዋጃ አንቀጽ ፴፱ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ያቋቋመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና የመሥሪያ ቤቱን ሃላፊዎች ወይም ተወካዮች ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

## ፳. <u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መረጃዎችን በቦርዱ ሲጠየቅ በሰነድ የተረጋገጠ የጽሁፍ መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፪/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት የተጠየቀውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የሰጠው መረጃ ሃሰት መሆኑን እያወቀ የሰጠ ከሆነ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱/፩//መ/ የተደነገገውን እርምጃ ከመውሰዱ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

## ፳፩. <u>የአመራር አባላትን ስለማሳወቅ</u>

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አዲስ የአመራር አባላትን የመረጠ እንደሆነ ወዲያውኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

፪/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በተለያየ ምክንያት የአመራር አባላቱ የተጓደሉ ከሆነና ቁጥሩም ከ፶፻+፩ በታች ከሆነ በ፴ ቀናት ውስጥ ማሟላት አለበት። ይህንንም ወዲያውኑ ለቦርዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

## ፳፪. <u>ስለፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች አጠባበቅ</u>

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ክፍል አምስት ምዕራፍ ሁለት በተመለከቱት ጉዳዮች ማለትም እንደ ሂሳብ መዝገብ፣ የስጦታ ሰርተፊኬት፣ የባለንብረትነት መረጃ ሰነዶች እና የመሳሰሉትን በሚገባ የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም በቦታው መጣበብና በሠራተኛ እጥረት ምክንያት ከ፲ ዓመታት ዕድሜ በላይ ያላቸው የሂሳብ ሰነዶች ማስወገድ ይችላል።

4) Where a political party has not given informations and explanations as are required by the provision of Article 9(4) of this Proclamation, it shall be liable inaccordance with Article 39 of this Proclamation.

5) A political party that established branch office in accordance with Article- 17 of this Proclamation shall notify in writing to the Board as to the address and leaders or representatives of the office.

## 20. <u>Duty to Provide Information</u>

1) Every political party is under obligation to give a written information certified by a document when the Board requires such informations as are provided under this Proclamation.

2) Where a political party required to give information pursuant to sub article (1) of this Article is unwilling to provide such information or gives intentionally untrue information, in addition to the measures of the Board under Article 39(1) (d) of this Proclamation the party shall be liable under the appropriate law.

## 21. <u>Notification of Leading Members</u>

1) Every political party shall notify immediately to the Board when it elects new leading members.

2) When leading members of a political party vacate on various reasons and such number is below 50%+1, the party shall elect in their place another members with in 30 days. The party shall immediately inform the same to the Board in witting.

## 22. <u>Keeping Documents of Political Parties</u>

1) Every political party shall have the duty to keep properly the matters provided under Chapter Two of Part Five of this Proclamation such as, books of account, certificates of donation, documents evidencing ownership and other similar documents.

2) Notwithstanding the provision of sub article (1) of this Article, based on the reasons of lack of space and manpower, books of accounts aged over 10 years may be disposed.

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፓርቲውን ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ጠብቆ መያዝ አለበት።

## ፳፫. ስለፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠ የሞያ ብቃት ያለው የውጭ ኦዲተር ይሾማል።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ የተገለፀው የፖለቲካ ፓርቲው ኦዲተር ሹመት በፓርቲው ህገደንብ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀፅ መሠረት የተሾመ ኦዲተር ሹመቱን መቀበሉን በፊርማው ማረጋገጥ አለበት።

፬/ በተለያየ ምክንያት ኦዲተሩ ሥራውን ሲለቅ እና አዲስ ኦዲተር ሲተካ የፖለቲካ ፓርቲው መሪ አዲስ የተሾመውን ኦዲተር በ፴ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

## ፳፬. የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር መብት

በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተር ማንኛውንም ከፖለቲካ ፓርቲ ሀብትና ንብረት ጋር የተያያዘ ሰነድ በማንኛውም ጊዜ የማግኘት እና የመመርመር መብት አለው።

## ፳፭. የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር ሆኖ ሊሾም ስለማይችል ሰው

ማንኛውም ሰው የፓርቲው ጠበቃ፣ ተቀጣሪ፣ የቦርድ አባል በመሆን አገልግሎት ወይም እያገለገለ ከሆነ ወይም በማንኛውም መልኩ ከሿሚው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያለው ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲው ኦዲተር ሆኖ ሊሾም አይችልም።

## ፳፮. በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተር አሰራር

፩/ በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተርም ሆነ እርሱ ቀጥሮ ያሰማራቸው ባለሞያዎች ስራቸውን በቅንነት፣ በታማኝነትና በገለልተኝነት ማከናወን አለባቸው።

፪/ በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተር የኦዲት ሪፖርት በጽሁፍ ሆኖ ለፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች መሰጠት አለበት።

3) Without prejudice to sub article (1) and (2) of this Article, every political party shall keep other documents properly.

## 23. Auditor of Political Party

1) Every political party shall appoint external auditor whose professional competency approved by the legally appropriate body.

2) The appointment of the political party auditor, provided in sub – article 1 of this Article, shall be concluded inaccordance with the by laws of the party.

3) The auditor appointed in accordance with this Article shall prove his acceptance of the appointment by his signature.

4) The leader of the political party shall notify the Board with in 30 days as to the appointment of new auditor whenever based up on various reasons the auditor leaves his office and replaced by a new one.

## 24. Right of Political Party Auditor

The auditor appointed by a political party shall have the right to find and examine at any time any document related with the assets and properties of the political party.

## 25 A Person Incapable of Appointment as Political Party Auditor

Whosoever served or serving a political party as lawyer, employee, board member, or whosoever in any manner relates with the appointing political party, might not be appointed as the political party auditor.

## 26 Organization of Work of Appointed Auditor of Political Party

1) The auditor appointed by a political party and also his professional employees engaged at tasks provided by him shall perform their respective work ethically, honestly and neutrally.

2) The audit report of the auditor appointed by a political party shall be made in writing and be submitted to the political party leaders.

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው ከሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ጋር የኦዲተሩ የሞያ ብቃት ሰርተ ፊኬት ተያይዞ መቅረብ አለበት።

## ፳፯. ስለፖለቲካ ፓርቲ ስያሜና አርማ

፩/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ስያሜ ከተመ ሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የንግድና ኢንዳስትሪ ሥራዎች ድርጅት ወይም ሌላ ማሕበራዊ ተቋም ወይም ከግለሰብ ስም ጋር የማይመሳሰል ወይም የማያደናግር የፓር ቲው ብቸኛ መጠሪያ መሆን አለበት።

፪/ የፓርቲው ዓርማ እና ሰንደቅ ዓላማ፤

ሀ/ ከሌሎች ፓርቲዎች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ጋር የማይመሳሰል፣

ለ/ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማ ኖት መካከል ጥላቻና ግጭትን የማይፈጥር፣

ሐ/ የጦረኝነትን ወይም ሌላ ሕገወጥ ድርጊትን መልዕክት የማያስተላልፍ፣

መ/ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወይም ዓርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣

ሠ/ የሕዝብን ሞራል፣ ሥነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይነካ መሆን አለበት።

# ምዕራፍ ሦስት
# የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ

## ፳፰. በፖለቲካ ፓርቲ የመሳተፍ መብት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በፓርቲው ስብሰ ባዎች ላይ የመሳተፍ፣ ሐሳቡንና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፣ ድምፅ የመስጠት እና መምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አለው።

## ፳፱. ስለአባልነት መዋጮ

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው በሚወስነው መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲው በየጊ ዜው የአባልነት መዋጮ ሊከፍል ይችላል።

3) The audit report to be submitted by a political party shall be attached with the certificate of professional competency of the auditor.

## 27. Designation and Emblem of Political Party

1) The designation of any political party shall be the sole designation of the party and shall not be similar to or create confusion with the designation of another political party or commercial and industrial organization or social institution or individual.

2) The emblem and flag of the party shall not have to:

a) be similar with the emblems and flags of other political parties;

b) create hatred and conflict among nation, nationalities, race, religion;

c) convey messages of war and other unlawful activities;

d) be similar with the flag or emblem of Ethiopia or with those of the various international organizations or with the symbols of religion organizations;

e) be against ethics or public morality or other similar public interests.

# CHAPTER THREE
# RIGHTS AND OBLIGATIONS OF MEMBERS OF A POLITICAL PARTY

## 28. Right of Participation

Any member of a political party shall have, in accordance with the by laws of the party, the right to participate in the meetings of the party, to express freely his views and comments, to vote and to elect or to be elected.

## 29 Membership Dues

A member of a political party may pay membership dues periodically to the political party inaccordance with the by-laws or decisions of the political party.

**፴. ከአባልነት ስለመወገድ**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የፖለቲካ ፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ከአባልነት ሊወገድ ይችላል።

፪/ ከፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ከፓርቲ አባልነት የተወገደ አባል በውሳኔው ላይ ቅሬታ ሲኖረው መወገዱ በተገለጸበት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

**፴፩. ስለአባልነት**

፩/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መስራቾቹና ከምስረታ በኋላ የፓርቲው አባላት የሆኑትን ያካተተ ነው።

፪/ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ተላልፎ የማይሰጥ በአባሉ ላይ ተወስኖ የሚቀር ነው።

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማን ኛውም ጊዜ አባልነቱን ሊተው ይችላል።

፬/ የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች መቃረን የለበትም።

**ክፍል አራት**
**ስለፖለቲካ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር፣ መቀናጀት፣ መተካት እና መሰረዝ**

**ምዕራፍ አንድ**
**ስለፖለቲካ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር፣ መቀናጀት እና መተካት**

**፴፪. ስለፖለቲካ ፓርቲ ውህደት**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዋህደው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ይችላሉ።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለመዋሃድ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን የጠቅላላ ምርጫ ወይም የአካባቢ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ ከ፴ ቀናት በፊት በፅሁፍ ለቦርዱ ያቀርባሉ፣ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረትም ምዝገባው በቦርዱ ይፈፀማል።

፫/ ለውህደት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተ ሉትን ማካተት አለበት፤

**30. Expulsion from Membership**

1) A member of a political party may be expelled from membership to be determined in accordance with the by laws of the political party.

2) Where a member is expelled from party membership contrary to the by laws of the party, the member may file a petition at the Federal High Court with in three months from the date of the notification of such decision of expulsion.

**31. Membership**

1) Any political party shall have members including the founders and members admitted after the formation of the party.

2) Membership of a political party may not be devolved by succession or by any other manner to another person, and shall be limited to the member in person.

3) A member of a political party may at any time withdraw from his membership.

4) The by – laws of a political party may not contradict the provisions of this Chapter.

**PART FOUR**
**UNION, FRONT, COALITION, SUBSTITUTION AND CACELLATION OF POLITICAL PARTIES**

**CHAPTER - ONE**
**UNION, FRONT, COALITION AND SUBSTITUTION OF POLITICAL PARTIES**

**32. Union of Political Parties**

1) Two or more political parties registered in accordance with this Proclamation may unite and form a political party.

2) Political parties wished to unite pursuant to sub article (1) of this Article shall submit their proposition in writing to the Board 30 days before the issuance of time schedule for local or general election; as a result the registration shall be effected in accordance with the provisions of this Proclamation.

3) The application for union shall consist the following:

ሀ/ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው ጉባኤ ውህደቱን የተቀበለ ስለመሆኑ የሚገልፅ ውሳኔ እና

ለ/ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሲዋሃዱ የሚኖረ ውን አዲስ ስምና በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ የተዘረዘሩ ሰነዶችን።

፬/ ቦርዱ በዚህ ህግ መሠረት የውህደት ጥያቄ ውን የተቀበለው ከሆነ፤

ሀ/ ለእያንዳንዱ ለተዋሃዱት የፖለቲካ ፓር ቲዎች ተሰጥቶ የነበረውን የምዝገባ የም ስክር ወረቀት ይሰርዛል፣ አዲሱ ፓር ቲም በዚህ ህግ መሠረት ይመዘገባል፤

ለ/ ቦርዱ የእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ንብ ረት፣ ገንዘብና አስፈላጊ ሰነዶች በው ህደት ወደ ተመሰረተው የፖለቲካ ፓርቲ በ፮ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲተላለፍ ትዕዛዝ ይሰጣል።

፭/ በውህደት የሚመሠረት የፖለቲካ ፓርቲ እን ደሁኔታው የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭ ወይም አንቀጽ ፮ መስፈርት ማሟላት አለበት።

፮/ ማንኛውም ከዚህ በፊት የወንጀል ክስ ያለ በት የፖለቲካ ፓርቲ ክሱ ሳይዘጋ ሊዋሀድ አይችልም።

## ፴፫. <u>የፖለቲካ ፓርቲ መዋሀድ የሚያስከትለው ውጤት</u>

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪/፬/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውህደት ውጤት የሆነው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወራሽ ይሆናል፣

ለ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች መብትና ግዴታ ይተላለፍለታል፣

ሐ/ የተዋሃዱትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለፈ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በቦርዱ ሲጠየቅ ያቀርባል፣

መ/ ከዚህ በፊት እያንዳንዱ የተዋሃዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለባቸውን ፍርድ ወይም መብት ወይም በፍርድ ቤት በሂደት ያለን የፍተሃብሔር ወይም የአስተዳደራዊ አካል ክርክር ተተክቶ ያስፈጽማል፣ ይፈጽማል።

a) a decision expressing acceptance of the union by the assembly of each constituent parties of the union; and

b) the new designation resulted by the union of the poitical parties, and the documents listed under Article 8 of this Proclamation.

4) If the Board accepts, in accordance with this Proclamation, the application for union, then the Board shall:

a) cancel and register, in accordance with this Proclamation, the registration certificate of each constituent political parties of the union and the new party respectively;

b) order the transfer of each political party's property, money and other necessary documents to the party created by the union with in 6 months.

5) The political party created by the union shall fulfill the requirements of Article 5 or Article 6 of this Proclamation conditionally.

6) A political party charged with crime may not unite before its criminal charge come to an end.

## 33. <u>Effects Resulted by Union of Political Parties</u>

1) Without prejudice to Article 32(4) of this Proclamation, the new political party resulted from union:

a) shall be successor of the political parties constituted the union;

b) rights and duties of the political parties constituted the union shall be transferred to it;

c) shall submit report on the past financial activity of the political parties constituted the union, where asked by the Board;

d) shall execute or cause the execution of decision or right or disputes of civil or administrative body pending at court previously concerned with each or either constituent political parties of the union.

፪/ የውህደቱ ውጤት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በተመዘገበ በ፮ ወር ጊዜ ውስጥ ውህደቱ ያስገኘውን ሀብት፣ ንብረትና እዳ የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ እና ፶፮ መሠረት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

## ፴፬. ግንባር ስለመፍጠር

፩/ የራሳቸው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና አባላት ያላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ግንባር መፍጠር ይችላሉ።

፪/ ግንባር ለመፍጠር የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ/ እያንዳንዱ ፓርቲ የግንባሩን ምስረታ የተቀበለ መሆኑን የሚገልፅ የጉባኤ ውሳኔ፣ እና

ለ/ ግንባሩ የሚኖረው ስም እና በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ የተዘረዘሩ ሰነዶችን።

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት ግንባር ለመፍጠር የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን ለቦርዱ በፅሁፍ ያቀርባሉ፣ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረትም ምዝገባው በቦርዱ ይፈፀማል።

፬/ ቦርዱ ህግ መሠረት የግንባር ምሥረታውን ጥያቄ የተቀበለው ከሆነ፤

ሀ/ የግንባሩ አባል ድርጅቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሳይሰረዝ ለግንባሩ ሌላ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

ለ/ የእያንዳንዱ የግንባሩ አባል ድርጅቶች የራሳቸው ሀብትና ንብረት እንደተጠበቀ ሆኖ ግንባሩ የራሱ ሀብትና ንብረት ይኖረዋል።

፭/ ግንባር ሆኖ የተመሰረተ የፖለቲካ ፓርቲ እንደሁኔታው የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭ ወይም አንቀጽ ፮ መስፈርት ማሟላት አለበት።

## ፴፭. ስለፖለቲካ ፓርቲ መቀናጀት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜ እና በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ተቀናጅተው እንደሁኔታው በሃገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ።

2) The new political party resulted from the union and registered in accordance with this Proclamation shall submit to the Board within 6 months of its registration a financial report according to Article 54 and 56 of this Proclamation showing the asset, property and debt bring about by the union.

## 34. Formation of Front

1) Two or more political parties having their own program, by – laws and members may form a common front.

2) The application for formation of front shall consist the following:

a) a decision expressing acceptance of the front formation by the assembly of each constituent parties of the front; and

b) the designation of the front, and the documents listed under Article 8 of this Proclamation.

3) Political parties wished to form a front pursuant to sub article (1) of this Article shall submit their proposition in writing to the Board; as a result the registration shall be effected in accordance with the provisions of this Proclamation by the Board.

4) If the Board accepts, in accordance with this Proclamation, the application for the formation of front:

a) without canceling the certificate of registration of member parties of the front, the Board shall give another certificate of registration to the front;

b) without prejudice to the assets and properties of each constituent political parties of the front, the front shall have its own asset and property.

5) The political party formed as front shall fulfill the requirements of Article 5 or 6 of this Proclamation conditionaly.

## 35. Coalition of Political Parties

1) Two or more political parties registered in accordance with this Proclamation may, for a limited period and specified objectives, form coalition to act at country- wide or regional level up on condition.

፪/ ተቀናጅተው ለመንቀሳቀስ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው የፖለቲካ ፓርቲው ከፍተኛ አመራር የተስማማበት መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ በማያያዝ የፅሁፍ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው። ቦርዱ ጥያቄውን ከተቀበለው ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል።

፫/ ለመቀናጀት የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ እንቅስቃሴ የስምምነት ነጥቦችን የያዘ ሰነድ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

፬/ በዚህ አንቀፅ የተደነገገው ቢኖርም እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ህጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቀጥላል።

**፴፮. ስለ ፖለቲካ ፓርቲ መተካት**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው ጉባዔ ውሳኔ ስሙንና ፕሮግራሙን ለውጦ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገብ ይችላል።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት በአዲስ የተቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲ የፈረሰው የፖለቲካ ፓርቲ ሀብት እና ንብረት ይተላለፍለታል።

፫/ አዲስ አተተካው የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት።

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ

**፴፯. የፖለቲካ ፓርቲን ከመዝገባ ስለመሰረዝ**

የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰረዝ ይችላል፤

፩/ በፓርቲው ህገደንብ መሠረት በራሱ ፈቃድ ከምዝገባ እንዲሰረዝ ሲጠይቅ፣

፪/ በህግ መሠረት ቦርዱ ሲወስን ወይም

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው ከምዝገባ እንዲሰረዝ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥ።

2) Political parties wished to act by forming coalition shall submit to the Board a written application attached with a document expressing the agreement of each political party respective higher leader. Where the Board accepts the application, it may give temporary certificate.

3) Political parties wished to form coalition shall submit to the Board a document consisting the points of agreement concerning their common activity.

4) Notwithstanding the provision of this Article, each political party of the coalition shall continue to exist with its legal personality.

**36. Substitution of Political Party**

1) Any political party may be registered as a new political party by changing its name and program up on the decision of the party assembly.

2) The asset and property of the dissolved political party shall be transferred to the new political party established in accordance with sub article (1) of this Article.

3) The new substituted political party shall have to be registered in accordance with this Proclamation.

## CHAPTER TWO
## CANCELLATION AND DISSOLUTION OF POLITICAL PARTY

**37. Canceling the Registration of Political Party**

A political party may be cancelled in one of the following reasons:

1) when the party, according to its by-laws, consent and request to be canceled;

2) when the Board decides on basis of law; or

3) when the court decides the registration of the political party to be canceled.

**፴፰. በፖለቲካ ፓርቲው ጥያቄ ከምዝገባ ስለመሰረዝ**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በህገደንቡ መሠረት ራሱ ከፖለቲካ ፓርቲነት እንዲሰረዝ ቦርዱን በፅሁፍ ሊጠይቅ ይችላል።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት የቀረበ የመሰረዝ ማመልከቻ በፓርቲው መሪ የተፈረመ መሆን ይገባዋል።

፫/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ ከተገለፀው ማመልከቻ ጋር የሚከተለ ውን አያይዞ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲውን የኦዲት፣ የሃብትና ንብረት ሪፖርት፣እና

ለ/ ስለፓርቲው መፍረስ በፖለቲካ ፓርቲው ጉባዔ የተወሰነበትን ሰነድ።

፬/ ከፖለቲካ ፓርቲነት ለመሰረዝ ማመልከቻ ባቀረበ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ተቃ ውሞ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ ያለው ማን ኛውም ሰው ተቃውሞ ማቅረብ እንዲችል ቦርዱ የመሠረዝ ማመልከቻ መቅረቡን በተለያየ የማስታወቂያ መንገድ ለሕዝብ ይገልፃል።

፭/ ከላይ ንዑስ አንቀፅ /፬/ መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ፲፬ ቀን ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ ይኖር በታል። ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲውን አይሰርዝም።

፮/ በዚህ አንቀፅ መሰረት ቦርዱ የመሰረዝ ማመ ልከቻውን ከተቀበለው በ፴ ቀናት ውስጥ ለጠ ያቂው ፓርቲ ስለመሰረዙ በፅሁፍ ያሳው ቃል። የፓርቲውን መፍረስም ሕዝብ እንዲ ያውቀው ያደርጋል።

**፴፱. የፖለቲካ ፓርቲን በቦርዱ ውሳኔ ከምዝገባ ስለመሰረዝ**

፩/ ቦርዱ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ ሊሰርዝ ይችላል፤

**38. Canceling Registration up on the Request of the Political Party**

1) A political party may, according to its by-laws, request the Board in written form that its registration be cancelled.

2) The statement of application for cancellation presented as according to sub – article (1) of this Article shall be signed by the party leader for its validity.

3) The political party shall attach the following particulars with its application to the Board as referred in sub article (1) of this Article and

a) he political party's audit, asset and property report; and

b) the document in which the assembly of the political party decided to dissolve the party.

4) The Board shall announce, as to the application for cancellation submitted to it, to the public through various means of information, to enable any person present its objection where that person has opposition or a claim against the political party presented the application for cancellation.

5) A person who has an objection pursuant to sub article (4) of this Article, shall present the objection to the Board with in 14 days from the date of announcement; within such period the Board shall not cancel the political party.

6) Where the Board accepts, in accordance with this Article, the application for cancellation, it shall notify in writing the requesting party within 30 days as to its cancellation; the Board shall also notify the public as to the dissolution of the party.

**39. Canceling Registration of Political Party upon the Decision of the Board**

1) The Board may cancel the registration of a political party in one of the following reasons:

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የስም፣ የመለያ ምልክት፣ የሰነድ፣ የአመራር፣ የኦዲተር፣ የዋና ጽሕፈት ቤት እና የመሳሰለውን ለውጥ ሲያደርግ በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ፣

ለ/ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ እንዲያቀርብ የተደነገገውን አመታዊ የስራ፣ የሂሳብ፣ ወይም ሌሎች ወቅታዊ ሪፖርቶች ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣

ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲው ለሁለት ተከታታይ የምርጫ ዘመን የጠቅላላ ወይም የአ ካባቢ ምርጫ ውድድርን ሳይሳተፍ የቀረ እንደሆነ፣

መ/ የፖለቲካ ፓርቲው አጭበርብሮ ወይም አሳሳች መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ከሆነ ወይም በዚህ ህግ መሠረት መረጃ ሲጠየቅ የሃሰት መረጃ ለቦርዱ የሰጠ እንደሆነ።

፪/ ቦርዱ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ሲያምን ፓርቲው ስህተቱን እንዲያስተካክል የፅሁፍ ማስጠን ቀቂያ ይሰጠዋል። በማስጠንቀቂያው መሠ ረት ያላስተካከለ እንደሆነ ከምዝገባ ሊሰ ርዘው ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀፅ መሠረት ቦርዱ ያሳለፈውን ውሳኔ የተቃወመ የፖለቲካ ፓርቲ ውሳ ኔው በደረሰው በ፲፬ ቀናት ውስጥ ይግባ ኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

## ፵. የፖለቲካ ፓርቲን በፍርድ ቤት ውሳኔ ስለመሰረዝ

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ህገ-መንግሥቱን፣ ይህንን አዋጅና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች በመጣስ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይፈርሳል።

፪/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በፈጸመው ከባድ ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በሚሰጠው ውሳኔ ከፖለቲካ ፓርቲ ነት ሊሰረዝ ይችላል።

a) the political party has not notified the Board according to the provisions of this Proclamation when it changes its name, emblem, document, leadership, auditor, head office and other similar change;

b) the political party fails to submit to the Board, as required by the provision of this Proclamation, annual performance, audit, or other periodical reports;

c) the political party fails for two successive election terms to participate at general or local elections;

d) the political party has been registered by fraud or by presenting deceitful document, or when requested pursuant to this Proclamation, the political party submits to the Board a false document.

2) The Board may give a written notice reminding the party to conform to the law, when it ascertains that the political party has violated the provisions of this Proclamation. If the political party fails to conform according to the notice, the Board may cancel the registration of the party.

3) A political party that objects the decision of the Board according to this Article may appeal, within 14 days from receiving such decision, to the Federal High Court.

## 40. Canceling a Political Party up on Court Decision

1) A political party acting in violation of the provisions of the Constitution, this Proclamation and other laws of the state shall be dissolved up on the order of the court.

2) A political party may be cancelled due to its serious criminal charge as a result of the court decision.

፫/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ የቀረበበትን የፖለቲካ ፓርቲ ጥፋተኛ ሆኖ ሲያገኘው እንደወንጀሉ ክብደት በወንጀል ህጉ መሠረት በማስጠንቀቂያ ሊያልፈው፣ ለተወሰነ ጊዜ የፖለቲካ ስራውን ከማንቀሳቀስ ሊያግደው ወይም ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰርዘው ወይም ሊቀጣው ይችላል።

**፵፩. <u>የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ ውጤት</u>**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ወይም በቦርዱ ውሳኔ እንዲፈርስ ሲወሰን የፓርቲው ንብረት ላለበት ዕዳ መሸፈኛ ይውላል።

፪/ የፖለቲካ ፓርቲው ዕዳ የሌለበት ከሆነ ወይም ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት እዳውን ሸፍኖ ቀሪው ገንዘብና ንብረት በቦርዱ ትእዛዝ ለሥነ ዜጋና መራጮች ትምህርት እንዲውል ይደረጋል።

፫/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ፓርቲው ያለው ገንዘብና ንብረት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል።

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>ስለፖለቲካ ፓርቲዎች የገቢ ምንጭ እና የንብረት ሁኔታ</u>**

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ከመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ</u>**

**፵፪. <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>**

፩/ መንግሥት በፌዴራልና በክልል ምክር ቤቶች ውክለና ላላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የዕለት ተዕለት ሥራ ማከናወኛ ድጋፍ ይሰጣል።

፪/ መንግሥት ለፌዴራል ወይም ለክልል ምክር ቤቶች የምርጫ ተግባር የሚውል ድጋፍ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ይሰጣል።

፫/ መንግሥት በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ድጋፍ በገንዘብ፣ በዓይነትና በአገልግሎት ሊሆን ይችላል።

፬/ ስለመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም በምርጫ ህጉ በተደነገገው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

3) Where the Federal High Court found the accused political party guilty of the criminal charge, the Court may, on the basis of the seriousness of the crime according to the Criminal Code, give warning notice or suspend the party for a specified period from political activity or cancel the registration or penalize the party.

**41. <u>Effect of Cancellation or Dissolution of Political Party</u>**

1) Where a political party dissolved by its own decision or by the Board decision, the property of the party shall be expended to cover its debt.

2) Where the political party owes no debt or where there remains an amount after covering the debt as referred in sub article – (1) of this Article, the property or the remaining amount shall be expended to civic and electorate education up on the order of the Board.

3) Where a political party is cancelled or dissolved by decision of the court, the money and property of the party shall be transferred to the government up on the order of the court.

**<u>PART FIVE</u>**

**<u>SOURCE OF INCOME AND PROPERTY AFFAIRS OF POLITICAL PARTIES</u>**

**<u>CHAPTER - ONE</u>**

**<u>SUPPORT GRANTED FROM GOVERNMENT</u>**

**42. <u>General Provision</u>**

1) The government may grant support for political parties that have representation at the Federal and at State houses for conducting their day to day activity.

2) The government may grant support to political parties to be effected for election purpose for federal or state houses.

3) The support to be granted by the government according to this Article may be in the form of money, in kind and in service.

4) The utilization of mass media shall be carried out in accordance with the election law.

**፵፫. በመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ ምንጭ**

በመንግሥት የሚሰጠው ድጋፍ፤

፩/ ከመንግሥት የሚመደብ፣

፪/ ከውጪም ሆነ ከሀገር ውስጥ ከሚገኝ ድጋፍ ወይም እርዳታ እና

፫/ ከሌላ ከማንኛውም አካል የሚመነጭ ነው።

**፵፬. መ ር ህ**

፩/ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ በፍትሃዊነት እና ያለ አድልኦ መፈጸም አለበት።

፪/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣ ቸውን ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር መዋላቸውን የሚያሳውቁበት የግል ጽነትና የተጠያቂነት መርህ መከተል አለባቸው።

**፵፭. የመንግሥት ድጋፍ የሚሰጥበት መስፈርት**

፩/ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጋፍ የሚከፋፈለው በፌዴራል ወይም በክልል ምክር ቤቶች ባላቸው መቀመጫ ብዛት መሠረት ይሆናል።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ለፌዴራል ወይም ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ተግባር የሚሰጥ ድጋፍ፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረቡትን ዕጩ ብዛት፣

ለ/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረቡትን የሴት ዕጩዎችን ብዛት፣ መሠረት በማድረግ የሚከፋፈል ይሆናል።

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ የሚሰጥ ድጋፍ፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የመንግሥት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሚያደርጉትን መስፈርቶች ሲያጓድል ይቋረጣል፣

ለ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ መጠቀም አይችልም፣

**43. Source of Government Support**

The support to be granted by the government has its sources:

1) from allocation by the government;

2) from domestic or foreign support or aid; and

3) from any other body.

**44. Principle**

1) The support to be granted to political parties by the government shall be rendered equitably and without discrimination.

2) The political parties shall follow transparent and accountable principle in order to notify that the support granted by the government has been utilized properly and for the intended purpose.

**45. Requirements for Government Support**

1) The support to be granted to political parties shall have to be apportioned between the parties on the basis proportional to their number of seats in federal or state houses.

2) Notwithstanding the provision of sub – article (1) of this Article, the support to be granted to purposes of election for federal or state houses shall be:

a) apportioned on the basis of the number of candidates nominated by the political parties;

b) apportioned on the basis of the number of women candidates nominated by the political parties.

3) The support to be granted to political party in accordance with sub article (1) of this Article:

a) shall be terminated when the political party fails to meet the requirements eligible for receiving the grant of government support;

b) from the date the political party failed to meet the requirements, the political party may not utilize the support already granted to it;

ሐ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ ተመላሽ ያደርጋል።

፬/ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጋፍ የሚከፋፈልበት ሁኔታና ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

**፵፮. ለፖለቲካ ፓርቲዎች የዕለት ከዕለት ተግባር ማከናወኛ የሚሰጥ ድጋፍ ስለሚመራበት አሰራር**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲ የሚሰጠውን ድጋፍ ለተመደበለት ተግባር ብቻ ማዋል አለበት።

፪/ የፖለቲካ ፓርቲ የዕለት ተዕለት ተግባር የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ/ የተለመደውን የፖለቲካ ፓርቲ የዕለት ተዕለት ተግባር፣

ለ/ የሕዝቡን የፖለቲካ ግንዛቤ ማዳበር፣

ሐ/ የፓርቲውን ዓላማ ለሕዝቡ ማስረጽ፣

መ/ ዜጎች በሀገሪቱ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው መቀስቀስ፣

ሠ/ በሕዝቡና በመንግሥት ተቋማት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲጠናከር ማድረግ።

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ከመንግሥት የተሰጠውን ድጋፍ በወጪ አርዕስት በመዘርዘር በኦዲተር የተረጋገጠ ወቅታዊ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

፬/ የፖለቲካ ፓርቲው ለዕለት ከዕለት ተግባር ማከናወኛ በመንግሥት ከተሰጠው ድጋፍ ያልተጠቀመበትን የመመለስ ግዴታ አለበት።

**፵፯. ለምርጫ ተግባር ከመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ የሚመራበት አሰራር**

፩/ መንግሥት በምርጫ ለሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድጋፍ ለፌዴራል ወይም ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ተግባር ብቻ መዋል አለበት።

c) from the date the political party failed to meet the requirements, the political party shall return the support already granted to it;

4) The manner and time of apportionment of the support to be granted to political parties shall be determined by the directive to be issued by the Board.

**46. The Rule Applicable to the Support Granted to Political Parties for Conducting their Day to Day Activities**

1) A Political party shall utilize the support granted to it only for the intended purpose.

2) The day to day activity of a political party includes the following:

a) the customary day to day activity of political party;

b) developing political consciousness of the public;

c) acquainting the public with the aims of the party;

d) agitation to enable citizens to have active participation in the political activity of the country;

e) strengthening harmonious relationship between the public and the government institutions.

3) The support granted by the government to the political party for conducting the day to day activity shall be reported periodically to the Board by the political party after listing the expenditure of the grant in expenditure heading and certified by the auditor.

4) Of the portion of the support granted by the government to the political party for conducting the day to day activity, the political party shall return the unutilized portion.

**47. The Rule Applicable to the Support Granted by Government for the Purpose of Election**

1) The support granted by government to political parties participating in election shall only be utilized for the purpose of election at federal or state houses.

፪/ ለምርጫ ተግባር የሚወጣ ወጪ ምን ምን እንደሚያካትት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፫/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫ ተግባር ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ በወጪ አርዕስት በመዘርዘር በኦዲተር የተረጋገጠ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

፬/ የፖለቲካ ፓርቲው ለምርጫ ተግባር ከመንግሥት ከተሰጠው ድጋፍ ያልተጠቀመበትን የመመለስ ግዴታ አለበት።

## ፵፰. የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ አያያዝ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ በመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ በተለየ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት፣

ለ/ ሂሳቡን በህግ መሠረት ማንቀሳቀስና ከተፈቀደለት ውጪ ወጪ ማድረግ የለበትም፣

ሐ/ የተሰጠውን ድጋፍ በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ አለበት፣

መ/ በፋይናንስ ህግ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከመንግሥት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምን ተግባር እንዳዋለ የሚያሳይ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

፪/ ኦዲተሩ የመረመረውን ሂሳብ ከህግ ውጭ ወጪ የተደረገ መሆን አለመሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ ላይ አስተያየት መስጠት አለበት።

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው የኦዲት ሪፖርቱን፤

ሀ/ ለፓርቲው የዕለት ከዕለት ተግባር ማከናወኛ የተሰጠውን ድጋፍ በሚመለከት የሚቀርብ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፫ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፣

ለ/ ለምርጫ ተግባር የተሰጠውን ድጋፍ በሚመለከት ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

2) The particulars to be included as expenditure for the purpose of election shall be determined in accordance with the directive to be issued by the Board.

3) The support granted by the government to the political parties for the purpose of election shall be reported periodically to the Board in the audit report by the political parties after listing the expenditure of the grant in expenditure heading and certified by the auditor.

4) Of the portion of the support granted by the government to the political party for the purpose of election, the political party shall return the unutilized portion.

## 48. Books of Account of Political Party

1) Any political party:

a) shall deposit the support granted by government in specific bank account;

b) shall transact the account according to the law and may not expend outside the allowed expenditure;

c) shall keep the granted support in specific books of account by listing under every expenditure heading;

d) shall submit audit report certified by auditor, according to finance law, specifying the mount granted by the government in the budget year and the particulars for which the money has been expended.

2) The auditor shall forward his comment in the audit report as to whether the account audited by him has been expended outside the legal scope.

3) The political party shall submit its report to the Board:

a) within 3 months from the end of the budget year if the report relates to the support granted to it for conducting its day to day activity;

b) within the period as determined by the Board if it relates to the report to be submitted as to the support granted for the purpose of election.

፬/ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከመንግሥት የተሰጠን ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ በማንኛውም ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መመርመር ይችላል፡፡

## ፵፱. ስለተጠያቂነት እና ቅጣት

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ ከታለመለት ዓላማ ውጪ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም የሀሰት የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር በተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሀ/ የሚሰጠው ድጋፍ እንዲቀነስ ወይም እንዲቋረጥ፣

ለ/ ፓርቲው በወንጀል ህግ መሠረት በገንዘብ እንዲቀጣ፣ እንዲታገድ ወይም እንዲፈርስ፣

ሐ/ ፓርቲው ከመዝገብ እንዲሰረዝ ወይም

መ/ የፓርቲው ኃላፊ ወይም ኃላፊዎች በገንዘብ ወይም በእስር እንዲቀጡ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተዘረዘሩት ቅጣቶች እንደሁኔታው በተደራራቢነት ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡

፫/ ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲ አላግባብ የወጣን ወጪ ክስ በመመስረት ወይም በማቻቻል ሊያስመልስ ይችላል፡፡

## ፶. ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት

፩/ ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገውን ድጋፍ አስመልክቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ሪፖርት፤

ሀ/ በበጀት ዓመቱ ለፓርቲዎች ድጋፍ እንዲውል በመንግሥት የተመደበው ንና ከሌላ ምንጭ የተገኘውን ጠቅላላ መጠን፣

ለ/ በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመደበውን የድጋፍ መጠን፣

ሐ/ ህግ በሚፈቅደው መሠረት በእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በበጀት ዓመቱ ወጪ የተደረገ የገንዘብ መጠን፣

4) The Federal Auditor General may at any time inspect political parties concerning the utilization of the support granted by government.

## 49. Responsibility and Penalty

1) Where a political party; utilizes the government grant outside the purpose of the support, or not submits report on the required time, or submits a false financial document, or is in default of the obligation in relation with the grant:

a) the support for the party may be declined or terminated;

b) the party may be, according to the criminal law, fined, suspended or dissolved;

c) the party may be cancelled from registration, or

d) the leader or leaders of the political party may be fined or sentenced.

2) The penalties provided in sub article (1) of this Article may be executed concurrently.

3) The political party not expending properly may be compelled by the Board, through set off or court suit, to return that amount of expenditure not utilized properly.

## 50. Submission of Audit Report to the House of Peoples' Representatives

1) The Board shall, within a short time after the end of the budget year, submit report to the House of Peoples' Representatives concerning the support granted to political parties. The report shall include:

a) the total amount of support allocated from government and from any other sources to the parties in the budget year;

b) the amount of support allocated to each political party in the budget year;

c) the amount of expenditure in the budget year by each political party as permitted by law;

መ/ በበጀት ዓመቱ የታየውን የሂሳብ ሚዛን ያካተተ መሆን አለበት።

፪/ ቦርዱ የሂሳብ ሪፖርቱን፣ መዝገቡን እና መግለጫውን ለዋናው ኦዲተር መላክ አለበት።

፫/ የሂሳብ ኦዲተር የሂሳብ ሪፖርት በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ሪፖርቱን ከዋናው ኦዲተር የሂሳብ መግለጫ ጋር በማያያዝ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት።

## ምዕራፍ ሁለት
## የገቢ ምንጭ

### ፶፩. የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ

፩/ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ፤

ሀ/ ከአባላቱ የሚሰበሰብ የአባልነት መዋጮ፣

ለ/ ቦርዱ አጥንቶ በሚያስቀምጠው ጣሪያ መሠረት በኢትዮጵያውያን ግለሰቦች እና ኩባንያዎች የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፣

ሐ/ ከአንቀጽ ፵፪ እስከ አንቀጽ ፶ በተደነገገው መሠረት ከመንግሥት ከሚሰጠው ድጋፍና ዕርዳታ፣

ሊሆን ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በመንግሥት ወይም በብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ፈቃድ የገንዘብ አቅሙን ለማጎልበት ቀጣይነት በሌለው መልክ ዝግጅቶችን በማደራጀት ገንዘብ ለማሰባሰብ ይችላል።

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ ፪ ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች መስራት አይችልም።

### ፶፪. ከመቀበል የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሰዎች ወይም አካላት የሚሰጥን ስጦታ ወይም እርዳታ መቀበል በጥብቅ የተከለከለ ነው፤

ሀ/ ከውጪ ሀገር ዜጎች፣

ለ/ ከውጪ ሀገር መንግሥት ወይም ከውጪ ሀገር የፖለቲካ ድርጅት፣

d) the balance of account resulted in the budget year.

2) The Board shall send the audit report, the books of account and the financial statement to the Auditor General.

3) The Auditor General shall send the audit report, within 30 days from the date he received the report, to the House of Peoples' Representatives by attaching the Auditor General's financial statement.

## CHAPTER - TWO
## SOURCE OF INCOME

### 51. Income Source of Political Party

1) The income source of a political party may be:

a) membership dues collected from members;

b) donations or grants by Ethiopian nationals and companies in accordance with the limit to be set by the Board on basis of its study;

c) the grant and support to be given by the government as provided from Article 42 to Article 50 of this Proclamation.

2) Without prejudice to the provision of this Article, a political party may, upon the approval of the government or regional state administration, collect money from the proceeds of events organized on non permanent basis to enhance its financial position.

3) Notwithstanding the provision of Article 7 (2) of this Proclamation, a political party which has attained legal personality may not directly or indirectly engage in commercial and industrial activities.

### 52. Prohibited Donation or Grant

1) Every political party is prohibited to accept donation or grant from the following persons or bodies:

a) foreign nationals;

b) foreign government or foreign political party;

ሐ/ ከበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣

መ/ ከሃይማኖት ድርጅት፣

ሠ/ ከፍርድ እስረኞች፣

ረ/ ከህገ-መንግሥቱ ውጭ ሥልጣን ለመያዝ ከተደራጀ ቡድን ወይም ሰው፣

ሰ/ ከሽብርተኛ ድርጅት፣

ሸ/ ምንጩ ያልታወቀ ስጦታ ወይም እርዳታ፣

ቀ/ ከመንግሥታዊ ድርጅት፣

በ/ አንድን ነገር ወደፊት ለማስፈጸም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ከህግ ውጭ ጥቅም ለማግኘት በማለም ከማንኛውም አካል ወይም ሰው የሚሰጥ ስጦታ ወይም እርዳታ።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ ከ/ሀ/ እስከ /በ/ የተከለከለን ስጦታ ወይም እርዳታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተቀበለ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ያገኘው ገንዘብ ወይም ንብረት ይወረሳል። እንደሁኔታው አግባብ ባለው ህግ ይጠየቃል።

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ በማንኛውም መንገድ የደረሰው እንደሆነ ስጦታውን ወይም እርዳታውን በተቀበለ በ፳፩ ቀናት ውስጥ ከተያያዥ መረጃዎች ጋር ለቦርዱ ገቢ ማድረግ አለበት።

**፶፫. <u>ከህግ ውጭ ስለተገኘ ሀብትና ንብረት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደለት ውጭ ገንዘብ፣ ወይም ማናቸውንም ንብረት፣ በስጦታ፣ በዳረጎት፣ በውርስ፣ በንግድና ኢንዳስትሪ ሥራ ወይም በማናቸውም መንገድ ተቀብሎ ቢገኝ ንብረቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል፣ አግባብ ባለው ህግም ይጠየቃል።

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>
## <u>ስለማህደር፣ ሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር</u>

**፶፬. <u>የፖለቲካ ፓርቲ ማህደርና ኦዲት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ ትክክለኛና ቋሚ ማህደር በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በአግባቡ መያዝ አለበት፤

c) welfare organization or non-governmental organization;

d) religious organization;

e) prisoners of law;

f) an organized group or person assuming state power in a manner other than that provided under the Constitution;

g) terrorist organization;

h) donation or grant having unknown source;

i) government organization;

j) donation or grant from any body or person for the execution of any future object conferred unappropriate benefit or for receiving unlawful benefit.

2) Where any political party receives directly or indirectly the donation or grant prohibited in paragraph /a/ to /j/ of sub article (1) of this Article, the received money or property shall be confiscated. The political party may be responsible under the appropriate law.

3) Where a political party happened to get in any way the donation or grant prohibited under sub article (1) of this Article, the party shall return the donation or grant to the Board together with related documents within 21 days from the date it received the donation or grant.

**53. <u>Unlawfully Acquired Asset and Property</u>**

Where a political party is found to have accepted, in a manner otherwise than provided in this Proclamation, money or any property in the form of donation, gratuity, inheritance or proceeds from commercial and industrial activity, or accepted in any way, the assets so received shall be confiscated up on the decision of the court and the party shall be held responsible under the appropriate law.

## <u>CHAPTER THREE</u>
## <u>RECORD, BOOK KEEPING AND AUDITING</u>

**54. <u>Record and Audit of Political Party</u>**

Every political party shall have to keep appropriately at its head office an accurate and permanent record which includes the following matters:

፩/ ማንኛውም በዓይነትም ሆነ በገንዘብ የሚደረግ መዋጮ፣ ስጦታ፣ እና ቃል የተገባ ስጦታ ወይም መዋጮ፣

፪/ ከዚህ የሚከተሉትን ያካተተ የሂሳብ መግለጫ፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲውን የገንዘብ ምንጭ፣

ለ/ መዋጮ ያደረገውን ወይም ስጦታ የሰጠውን ወይም ቃል የገባውን ሰው ስም፣

ሐ/ ቃል የተገባ መዋጮ ወይም ስጦታ ካለም የሚከፈልበትን ጊዜ፣ እና

መ/ አጠቃላይ የፖለቲካ ፓርቲውን የሂሳብ እንቅስቃሴ።

፫/ የፖለቲካ ፓርቲ ቋሚ ንብረቶች ዝርዝር፣ መቼ እና እንዴት በባለቤትነት እንደያዘው፣

፬/ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቦርዱ የሚፈልጋቸውን ሌሎች መረጃዎች።

## ፶፭. <u>የሂሳብ መዝገብ</u>

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጭ ሂሳብ ስርአት ይኖረዋል።

፪/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጭ ሂሳብ አያያዝ ስርአት በሂሳብ አያያዝ ልምድ ተቀባይነት ባለው መንገድ መሆን አለበት።

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማንኛውም ጊዜ ለስራ መሰናክል ሳይሆን አባል የሆነበትን የፓርቲውን የገቢና ወጭ ሂሳብ መረጃ የማግኘት መብት አለው።

፬/ ማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚያወጣቸው ወጪዎች ሁሉ ለፖለቲካ አላማው መዋላቸውን ለቦርዱ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት።

## ፶፮. <u>ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት</u>

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በየዓመቱ በራሱ ኦዲተር የሂሳብ ምርመራ ያካሂዳል። የፖለቲካ ፓርቲው በቦርዱ ከተመዘገበ ከ፮ ወር ጀምሮ የሚሳብ ሪፖርቱን የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሶስተኛው ወር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

1) any contribution or donation to be made in kind or money, and promised contribution or donation;

2) financial statement consisting the following:

a) income source of the political party,

b) the name of the person who made contribution or donation or promise;

c) the time by which the promised contribution or donation is payable if any; and

d) the general financial activity of the political party.

3) list of the fixed assets of the political party, and when and how they are owned by the political party;

4) other related matters required by the Board.

## 55. <u>Books of Account</u>

1) Every political party shall have accounting procedure relating to its revenue and expenditure.

2) The procedure of account of revenue and expenditure of every political party shall be in accordance with the generally accepted practice of accounting.

3) Every member of a political party shall have a right to seek at any time, without hindering the activity, information concerning the revenue and expenditure accounts of the political party of which he is a member.

4) Every political party shall have the responsibility to prove to the Board that its expenditures are spent for its political objective.

## 56. <u>Annual Audit Report</u>

1) Every political party shall undertake audit inspection annually by its auditor. Starting from 6 months of its registration, the political party shall submit its audit report to the Board on the third month after the end of each budget year.

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለቦርዱ የሚያቀርበው አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት፤

ሀ/ የገቢ መጠን እና የገቢ ምንጭ፣

ለ/ የወጪ ዝርዝር እና

ሐ/ ስለትክክለኛነቱ የፖለቲካ ፓርቲው መሪ ፈርሞበት በፓርቲው ማህተም የተረጋገጠ ሰነድን ያካተተ መሆን አለበት።

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የዓመት የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ በይፋ ያወጣል። ይህ የዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በቦርዱ ትዕዛዝ በውጭ ኦዲተር ተመርምሮ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይገባዋል።

፬/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ሪፖርት ቢያቀርብም ቦርዱ በተላከለት ሪፖርት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው ቦርዱ የውጭ ኦዲተር በመላክ ሂሳቡ እንዲመረመር ያደርጋል። ለዚህም የሚያስፈልገውን ወጭ የፖለቲካ ፓርቲው ይሸፍናል።

## ክፍል ስድስት
## የተከለከሉ ተግባራት እና የሚወሰዱ እርምጃዎች

### ፶፯. ዓላማን በህገወጥ መንገድ ማስፋፋት የተከለከለ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሃይል ወይም በማስፈራራት የፖለቲካ ዓላማውን ለማስረጽ ማንኛውንም ሰው ወይም ቡድን ማደራጀት ወይም ማሰልጠን ወይም ሰዎችን በግድ መመልመል በህግ ያስቀጣዋል።

፪/ ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ የተገለፀውን ተግባር የረዳ ወይም የተባበረ እንደሆነ አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል።

### ፶፰. በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመሳተፍ ስለማይችሉ ሰዎች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀፅ ፪ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ አይችሉም፤

ሀ/ ዳኛ፣
ለ/ የመከላከያ ሰራዊት አባል፣
ሐ/ የፖሊስ አባል።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ የተጠቀሱት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ ከፈለጉ የመንግሥት ስራቸውን መልቀቅ አለባቸው።

2) The annual audit report to be submitted to the Board by every political party shall include:

a) the amount and source of revenue;

b )list of expenditure; and

c) a document as to its authenticity the political party leader signed on it and attested by the party seal.

3) Every political party shall prepare and officially issue annual audit report. Such annual audit report shall have to be inspected and accepted by the external auditor to be appointed by the Board.

4) Where a political party fails to submit the report as referred in sub article 1 of this Article, or if it submits, the Board finds uncertainty; the Board may cause the inspection of the account by sending an external auditor. The political party shall incur the costs of such inspection.

## PART SIX

## PROHIBITIONS AND MEASURES

### 57. Prohibition of Extending Political Aims by Illegal Means

1) It shall be punishable by law where a political party with a view to introduce its political aims by force or duress, organizes or trains or recruits by coercion a person or group.

2) Any person or group who accomplices or cooperates to effectuate the act referred in sub article (1) of this Article shall be punishable under the appropriate law.

### 58. Persons Restricted From Membership of a Political Party

1) Notwithstanding the provision of sub article (2) of Article 4 of this Proclamation, the following persons may not be admitted in the membership of a political party:

a) judge;
b) member of the Defense Force;
c) member of the police.

2) The persons referred in sub article (1) of this Article shall have to leave their work as civil servant if they wished to be a member of a political party.

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /፩/ የተደነገገውን የጣሰ ሰው ከያዘው የመንግሥት ሥራ በራሱ እንደለቀቀ ይቆጠራል።

## <u>ክፍል ሰባት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### ፶፱. <u>መሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ እንደተመዘገበ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት መሟላት የሚገባውን ሰነድ ያላሟላ ፓርቲን እንዲያሟላ ሊያዝ ይችላል።

### ፷. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት።

### ፷፩. <u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ የሚረዳ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

### ፷፪. <u>የተሻሩ ህጎች</u>

፩/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፹፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፹፪/፲፱፻፹፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯዋል።

### ፷፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም ፲፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3) A person who violates the provision of sub article (1) of this Article shall be deemed to terminate his work by his own consent.

## <u>PART SEVEN</u>
## <u>MISELLANEOUS PROVISIONS</u>

### 59. <u>Transitional Provision</u>

Any political party established prior to the promulgation of this Proclamation shall be deemed registered. However the Board may order a party that fails to fulfill the required document in accordance with this Proclamation to fulfill the same.

### 60. <u>Duty to Cooperate</u>

Every person shall have the duty to cooperate for the implementation of this Proclamation.

### 61. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>

The National Election Board of Ethiopia is hereby authorized to issue regulation and directive for the implementation of this Proclamation.

### 62. <u>Repealed Laws</u>

1) Political Parties Registration Proclamation No. 46/1993 is hereby repealed by this Proclamation.
2) Political Party Registration (as amended) Proclamation No. 82/1993 is hereby repealed by this Proclamation.

### 63. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come in to force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa this 24th day of September, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**